# ገብረ ማርያም ትምህርት ቤት

የትምህርት ቤት የወላጆች ተወካዮች ቦርድ ምርጫ

ቀጣዮቹ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ናቸው፡-

- የስርአተ ትምህርት እና ትምህርት ተያያዥ ጥያቄዎች
- የትምህርት ፕሮጀክት፣ ህጎች፣ መግቢ ሰአት እና የትምህርት ዘመን፣ የትምህርት አመታዊ እቅድ፣ የሰራተኞች የስልጠና እቅድ

በምርጫው ላይ የሚከተሉት አስተያየቶች ይቀርቡበታል፡-

- የትምህርት መዋቅር ልማት ማእቀፍ ውስጥ የስታፍ አባላት ስንብት፣ የስራ መደብ ዝግጅት፣ የሰራተኛ ምደባ፣ የመዋቅር ለውጥ (ትራንስፎርሜሽን)፣ የተቋን የፕሮግራም ተግባራት (ስፖርት፣ ባህል ወዘተ...)፣
- የግል ንጽህና፣ የስራ አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ጉዳዮች፣
- የተማሪዎች ቅበላ እና የወላጆች መረጃ ልውውጥ እና የሊሴ ገብረ ማርያም ትምህርት ቤት አጠቃላይ ተሳትፎ መረጃዎች፣
- የትምህርት ቤት ጉዞዎች (ትሪፕ) እቅድ እና ፋይናንስ አደራረግ፣ የትምህርት እንቅስቃሴሶዎች፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ቅበላ እና እንክብካቤ፣

የበጀት እና የፋይናንስ መዛግብት ስልጣን ላለው ተቆጣጣሪ ቦርድ ይቀርባል።

አስተዳዳሪው ቦርድ በሚያስተላልፈው ውሳኔ አግባብ፣ በእራሱ ተነሳሽነት ወይም በርእሰ መምህሩ ጠያቂነት በገብረ ማርያም ትምህርት ቤት ዙሪያ አስተያየት ሊሰጥበት ይችላል።

*4 ወንበሮች ምትክ ምርጫ ይደረጋል (4 ተተኪዎች)፦ የእጩዎች ዝርዝር ማካተት የሚገባው ቢያንስ 2 እጩዎች (2 አሁን ያሉ እና 2 ምትኮች) እንዲሁም ቢበዛ 4 እጩዎች (4 አሁን ያሉ እና 4 ተተኪዎች) ሊያካትት ይገባል።*
*እያንዳንዱ ዝርዝር የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ወላጆችን ሊያካትት ይገባል (ወቅታዊው ዝርዝር የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ወላጆች ሊያካትት ይገባል)*

የድምጽ አሰጣጥ፦

እያንዳንዱ መራጭ ቀጣይ መብቶች አሉት

- ከላይ በተመለከተው የምርጫ መጀመሪያ ሰአት በምርጫው ቀን ምርጫው ጣቢያው ተገኝቶ ድምጽ መስጠት፣
- ወይም በቀጣይ መልእክት ዘዴዎች መሰረት ድምጽ መስጠት፣
    - የድምጽ መስጫ ካርድ፡ ወረቀቱ ሳይሰረዝ ወይም ሳይደለዝ፣ ለዚሁ በተዘጋጀ ፖስታ መለያ ቁጥር ወይም ምልክት ሳይደረግበት በፖስታ ከትቶ በመላክ ድም መስጠት። ይህ ፖስታ በሁለተኛ ፖስታ ውስጥ ገብቶ ይታሸጋል፣ እንዲሁም የትምህርት ቤቱ የፖስታ አድራሻ ይጻፍበታል። "የትምህርት ቤት የወላጆች ተወካዮች ቦርድ ምርጫ" ተብሎ ይጻፍበታል።፣ በጀርባው ላይ ደግሞ መራጩ ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ ይደረግበታል።
    - የፖስታ ድምጽ መልእክት በህጻናት በእራሳቸው ሊላኩ ይችላሉ፣ ፖስታው በርእሰ መምህሩ ጸሐፊ ዘንድ እንዲቀመጥ ይደረጋል።
    - ከላይ የተመለከተው መረጃ ያልተጻፈበት ፖስታ ሳይከፈት ውድቅ ይደረጋል፣ በመሆኑም በምርው ውጤት ላይ ቆጠራ ውስጥ አይካተትም።
- በትምህርት አዋጅ ቁጥር 29 በቀን 15/11/1996 ዓ.ም በተደነገገው አግባብ የወላጆች ምርጫ ላይ ተወካይ መሰየም አይፈቀድም።

ካላንደር

| አርብ፣ መስከረም 24 እኤአ | የምርጫ መግለጫ |
|---|---|
| ሰኞ ጥቅምት 04 እኤአ | ቢያንስ እስከ 10 ሰአት አመልካቾች ማቅረብ (ለርእሰ መምህር ጸሐፊ) |
| ሰኞ፣ ጥቅምት 11እኤአ | የእጩዎች ዝርዝር ህትመት እና ለወላጆች ምርጫ ካርድ ማደል |
| ሰኞ፣ ጥቅምት 18 እኤአ | ከ 10 በፊት የምርጫ ፖስታ መላክ |
| ማክሰኞ፣ ጥቅምት 19እኤአ | የድምጽ መስጫ ቀን (2 እስከ 10) እና ከ10.15-12.30 ድምጽ ቆጠራ |
| እሮብ፣ ጥቅምት 20እኤአ | ውጤት ይፋ ማድረግ |

የድምጽ መስጫ ጣቢያው ክፍት ሆኖ የሚቆየው ከ02፡00 እስከ 10፡00 ድረስ ሆነ፣ በአስተዳደር ህንጻ ውስ ወደሚገኘው አዳራሽ ለመግባት ወላጆች በቸርችል ጎዳና ባለው መግቢያ ይጠቀማሉ። መታወቂያ ይዘው ሊመጡ ይገባል።

እጩ ለመሆን የሚሹ ወላጆች ኢሜይላቸውን በቀጣይ አድራሻ ሊልኩት ይገባል፡ secretariatproviseurlgm@gmail.com